የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

ጥር 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን

## የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ

## ኦዲት ሪፖርት

የንግድ ውድድርና ሸማቾች ጥበቃ ባለሥልጣን የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አዋጅ፣ደንብ እና በተከታታይ በወጡ መመሪያዎች መሠረት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሃብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ ከዚህ ሪፖርት ጋር የተያያዙትን የ2011 በጀት ዓመት የሂሣብ ሪፖርቶች እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ/የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ባለሥልጠኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በባለሥልጣኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የባለሥልጣኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት
- የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ሪፖርት
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት
- የሂሣብ ማመዛዘኛ ሪፖርት
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት

በእኛ አስተያየት የሂሣብ ሪፖርቶቹ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ድረስ የተሰበሰበው ገቢ የተከፈለው ወጪ እና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የተከተሉ መሆኑን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ፡፡

**ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች**

ከአጠቃላይ በጀት ብር 35,851,180.00 ውስጥ ብር8,296,495.35 (23%) ሥራ ላይ ያልዋለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደመቀች ሞገስ
የፋይናንሻል ኦዲት ሥራ አስኪያጅ
22/5/2012